በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ፡-200871

ቀን፡-27/01/2014ዓ/ም

ዳኞች፡- እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- አቶ አባይነህ አለባቸው ፡- ጠበቃ የሽበር መልኬ ቀርበዋል

ተጠሪ፡- አቶ ሙሉጌታ አዳነ -ተወካይ ላንቺስል አዳነ ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ደቡብ ጎንደር ዞን ከፍኛ ፍርድ ቤት በተጀመረው ቤትና ይዞታን ለማስለቀቅ የቀረበውን ክርክር ተጠሪ ከሳሽ አመልካች 1ኛ ተከሣሽ በዚህ ክርክር ያልተጠሩት እማሆይ ታከለች ረታ 2ኛ ተከሣሽ እነ ወ/ሮ ነገሱ አለባቸው 4 ሰዎች ደግሞ ጣልቃ ገብ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የከተማ ቤትና ይዞታን በሚመለከት የቀረበ የመፋለም ክርክር የሚመለከት ሲሆን ተጠሪ ሰኔ 12ቀን2006ዓ/ም በተፃፈ ክሳቸው በወረታ ከተማ ቀበሌ 02 የቤት ቁጥር 042 የሆነውንና አዋሣኙ የተጠቀሰውን ቤት የተጠሪ እናትና አባት ቤት ቢሆንም ወላጆቹ ከሞቱ በኋላ ለአመልካቹ በአደራ ተሰጥቶት እየተጠቀመበት መሆኑን እንዲያስረክበው ቢጠይቀውም ሁለተኛ ተከሣሽ የነበረችዋ እማሆይ ታከለች ረታ መሬት ነው በሚል ምክንያት ለመልቀቅ ፈቃደኛ አለመሆኑን በመዘርዘር ቤቱን እንዲለቅለት እንዲወሰንለት ጠይቋል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

አመልካች ቀርቦ ቤቱ የተጠሪ እናትና አባት ሐብት ስላልሆነ ክስ ማቅረብ የሚያስችል መብትና ጥቅም የለውም ሲል የመጀመሪያ መቃወሚያና ተጠሪው ማስረጃ አለማቅረቡን የተጠሪ አባት የደም ችግር ስለነበረበት ለደህንነቱ ሲባል ከሚኖርበት ቤት የተሻለ መሆኑ ታምኖበትና ከእናታቸው ከእማሆይ ታከለች ረታ ጋር ተማክረው እንዲኖርበት በመደረጉ እንጅ የቤቱ ባለሃብት አለመሆኑን፣ የመብራትና ውሃ ደረሰኝ የቤት ባለሃብትነትን የማያረጋግጥ መሆኑን በመዘርዘር ቤቱ የአመልካች አባትና የእማሆይ ታከለች ረታ ሃብት ነው ሲል ተከራክሯል፡፡ የእማሆይ ስላልቀረቡ መልስ የመስጠት መብታቸው የታለፈ ቢሆንም በኋላ መሞታቸው ስለተረጋጠ ተተኪዎች ቀርበው መልስ ሰጥተዋል፡፡

ክርክሩ በዚህ ደረጃ ላይ እያለ ጣልቃ ገቦች ቀርበው ቤቱ የሁለተኛ ተከሣሽና የባለቤታቸው (የጣልቃ ገቦች አያት) መሆኑን እነርሱ ተሣታፊ ሣይሆኑ በወንድ አያታቸውን ድርሻ ላይ የሚደረገው ክርክር መብታቸውን እንደሚጎዳ በመዘርዘር መብታቸው እንዲከበርላቸው በመጠየቅ አመልካች ካቀረበው ክርክር ጋር ተመሣሣይነት ያለው ክርክር አቅርበዋል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ጣልቃ ገቦች የሚያቀርቡት አቤቱታ በይርጋ የታገደ ነው በክርክሩ ጣልቃ ለመግባት የሚያስችል መብትና ጥቅም የላቸውም እንዲሁም ክርክራቸው አመልካች ከሚያቀርበው ክርክር ጋር ተመሣሣይ በመሆኑ ውድቅ እንዲደረግለት ተከራክሯል፡፡ እማሆይ ታከለች ረታ በመሞታቸው አመልካችና ጣልቃ ገብ በክርክሩ ተተኪ ሆነው መልስ መስጠት እንዲፈቀድላቸው ጠይቀው ተፈቅዶላቸው መልስ ሰጥተዋል፡፡

ፍርድ ቤቱ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ክርክሩን ውድቅ ካደረገ በኋላ ግራ ቀኙ ያቀረቧቸው ማስረጃዎች ያረጋገጡትን ፍሬ ነገር እንዲሁም ጉዳዩ የሚመለከታቸው የተለያዩ የከተማው የመንግስት አካላት አጣርተው መግልጫ እንዲያቀርቡለት ትዕዛዝ ሰጥቶ የቀረበለትን መግለጫ አከራካሪው ቤትና ይዞታ የተጠሪ አባትና እናት ሃብት ነው ወይስ የአመልካች አባት የአቶ አለባቸው አድገህና የእማሆይ ታከለች ረታ የሚለውን ጭብጥ ይዞ መርምሯል፡፡ በዚህም መሰረት የአመልካች አባት ከ1953 ዓ/ም አከራካሪውን ይዞታ ገዝተው ቤት ለመስራት በ1963ዓ/ም ፈቀድ ጠይቀው የነበረ ቢሆንም በ1976ዓ/ም በማዘጋጃ ቤቱ በተደረገ ምሪት ይዞታውን የተጠሪው አባት የተመራው መሆኑ፣ የአመልካች አባት ከ1976ዓ/ም ጀምሮ ግብር ከፍለውበት የማያውቁ መሆኑን፣ ለአጎራባች ባለይዞታዎች በተሰጣቸው ካርታ ላይ የተጠሪ አባት መመዝገቡ መረጋገጡን የአመልካች አባት ከሞቱ በኋላ ሀሰተኛ የፍርድ ቤት ውሣኔ ተዘጋጅቶ ቤቱ በአመልካች እናት በሚች እማሆይ ታከለች ረታ ስም መመዝገቡንና የተጠሪ አባት ማሕደር ከማዘጋጃ ቤት እንዲጠፋ መደረጉን እንዲሁም የአመልካች ባለቤት ወረታ ከተማ ማዘጋጃ ቤት የምትሰራ ስለመሆኑ ተረጋግጧል በሚል አመልካች ይዞታውን ለቆ ለተጠሪ እንዲያስረክብ ወስኗል፡፡ ይህ ውሣኔ በየደረጃው በሚገኙት የክልሉ ፍርድ ቤቶች ስለፀና አመልካች መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ተብሎ እንዲታረምለት ይህን የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡

አመልካች ታሕሣስ 14ቀን 2013ዓ/ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታው ለክርክሩ መንስዔ የሆነው ይዞታ በአመልካች አባት የተገዛና ቤት የሰራበት ስለመሆኑ ሟች ከሞቱም በኋላ በእናታቸው ስም የተመዘገበ ስለመሆኑ

በማስረጃ ተረጋግጦ ሣለ በአጎራባች ይዞታ ላይና ውሃና መብራት ደረሰኝ ላይ የተጠሪ አባት መመዝገቡ የተመዘገበበት ሁኔታ ግምት ውስጥ ሣይገባ እንደ ባለሃብት መቆጠሩ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነው ተብሎ እንዲታረምለት ጠይቋል፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በስር ፍርድ ቤት አመልካች አከራካሪውን ቤት ለተጠሪ እንዲያስረክብ የተወሰነበት አግባብነት ከማስረጃ ምዘና መርህ አንፃር ተጣርቶ እንዲወሰን ታዞ ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በፅኁፍ ተለዋውጠዋል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ ሚያዚያ 6ቀን 2013ዓ/ም በተፃፈ መልሱ ማስረጃ የመመዘን ስልጣኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አለመሆኑንና በጥቅሉ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ የማስረጃ ምዘና ስህተት የተፈፀመበት አይደለም የሚልበትን ምክንያት በመዘርዘር የአመልካች የሰበር አቤቱታ ውድቅ እንዲደረግለት ተከራክሯል፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታውን የሚያጠናክር መልስ መልስ አቅርቦ ክርክሩ ተጠናቋል፡፡

ከፍ ሲል በአጭሩ የተመለከትነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን የስር ፍርድ ቤት በሰጠውና በየደረጃው በሚገኙት የክልሉ ፍርድ ቤቶች በፀናው ውሳኔ የተፈፀመ መሰረታዊ ማስረጃ ምዘና ስህተት መኖር አለመኖሩ ላይ መልስ ለመስጠት የግራቀኙኝ ክርክር ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋዎች ጋር በማገናዘበብ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

እንደተመረመረው ተጠሪ ባቀረበው ክስ በወረታ ከተማ የሚገኘውና ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት ከአባቱ በውርስ የተላፈለት ቢሆንም ተጠሪው የሁለተኛ ተከሳሽ እማሆይ ታከለች ረታ ነው በሚል የያዘበት መሆኑን በመዘርዘር እንዲለቅለት ጠይቋል፡፡ አመልካች በበኩሉ ተጠሪ አባቱን ተክቶ የውርስ ድርሻውን ከሚካፈል በስተቀር ቤቱ የተጠሪ አባት ሳይሆን የተጠሪ አያት የአመልካች አባትና የእማሆይ ታከለች ረታ በመሆኑ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክሯል፡፡ ጣልቃ ገቦችም ቀርበው ከአመልካች ጋር ተመሣሣይነት ያለው ክርክር አቅርበዋል፡፡

የስር ፍርድ ቤት አከራካሪው ቤትና ይዞታ ባለሃብት ማን ነው የሚለውን ጭብጥ ይዞ በግራቀኙንና ራሱ በሰጠው ትዕዛዝ ተጣርቶ የቀረበለትን ማስረጃ መዝኗል፡፡ በዚህም መሰረት የቀረቡት የግራ ቀኙ ምስክሮች በጥቅሉ እንደሚያቀርቡት ክርክር ያስረዱ ቢሆንም የወረታ ከተማ ማዘጋጃ ቤት አጣርቶ ባቀረበው ከመልስ በተጨማሪ ገለልተኛ የሆነው የዞኑ ስራና ከተማ ልማት መምሪያ ስጉዳዩ አጣርቶ እንዲያቀርብ ትዕዛዝ ተሰጥቶ ከአጎራባች ይዞታዎች ሰነድ እና የአካባቢውን ሕዝብ ጠይቆ ባቀረበው መልስ ይዞታውን የአመልካች አባት የተጠሪ አያት በ1953ዓ/ም ገዝተው በ1963ዓ/ም ቤት ለመገንባት ፈቃድ የጠየቁበት ቢሆንም በ1976ዓ/ም ይዞታው ወደ ሽንሻኖ ገብቶ ለተጠሪ አባት ተመርቶ ቤት የተሰራበትና ወደ ባህር ዳር እስከሚሔድ ድረስም የተጠሪ አባት በቤቱ ውስጥ ይኖር እንደነበር ማረጋገጡን በሌላ በኩል የአመልካች አባት ከሞቱ በኂላ ሐሰተኛ የፍርድ ቤት ሰነድ(ውሣኔ) ተዘጋጅቶ ግልፅ ባልሆነ መንገድ ይዞታው ወደ አመልካች እናት የተዛወረ መሆኑን በአንፃሩ የተጠሪ አባት ሰነድ ከማዘጋጃ ቤቱ እንዲጠፋ የተደረገ ስለመሆኑ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ስለተረጋጠ አመልካች ይዞታውን እንዲለቅ ተወስኗል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በድጋሚ አጣርቶና ተጨማሪ ማስረጃ አስቀርቦ ከመረመረ በኋላ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ አፅንቷል፡፡

ስለሆነም የስር ፍርድ ቤቶች የደረሱበት መደምደሚያና የሰጡት ፍርድ ተገቢነት በማስረጃ ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር አንፃር ሲመዘን መሰረታዊ የማስረጃ ምዘና መርሆዎችን መሰረት ያላደረግ ነው የሚያስብል ምክንያት ስላላገኘን ተከታዩን ውሣኔ ወስነናል፡፡

## <u>ውሣኔ</u>

1) የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 97966 ጥቅምት 17ቀን 2013ዓ/ም በጉዳዩ ላይ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም ሲል የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2) ይህ ክርክር ያስከተለውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

**ሄ/መ** **የማይነበብ የአምስት**

*ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*